ABCON – Research & Consulting
Social, marketing & opinion researchers

AFRO BAROMETER 1999-2019
20 years of giving voice to Africans

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ነሐሴ 19 2012 ዓ.ም

# ከጥናቱ ግኝቶች ፕሬስ ሪሊዝ

## ኢትዮጵያዊያን በፌደራሊዝም ስምምነት ቢኖራቸውም ብሄርን መሰረት ያድረግ ወይስ የመልካ-ምድር አቀማመጥ የሚለው ላይ ልዩነት እንዳላቸው የአፍሮ ባሮሜትር የጥናት ውጤት ያሳያል።

በአብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ ኢትዮጵያዊያን ምልከታ ፌደራሊዝም ራሳቸውን የቻሉ ክልሎች በማዋቀሩ ተመራጭ የመንግስት አስተዳደር እንደሆነ አዲሱ የአፍሮ ባሮ-ሜትር የጥናት ውጤት ያሳያል።

ሆኖም የፌደራሊዝሙ አወቃቀር አሁን እንዳለው የብሄር ማንነትን መሰረት ያደረገ የክልሎች አወቃቀር ይሁን ወይስ የሀገሪቷን መልካ-ምድር አቀማመጥ መሰረት ያደረገ ይሁን የሚለው ላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች በሁለት ተከፍለዋል።

በሀገሪቷ ባለፉት ሁለት ዓመታት የለውጥ እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በፌደራሊዝሙ እጣፋንታ ላይ ሰፋፊ ውይይቶችና ክርክሮች እየተደረጉ ይገኛል። የመንግስትና የግል ሚዲያዎች ለፖለቲከኞች፣ ለምሁራንና ለሲቪክ ማህበራት ህገ-መንግስቱ ከፀደቀበት 1995 እ.ኤ.አ ጀምሮ እየተተገበረ ያለው ብሄር/ ህብረ-ብሄራዊ ፌደራሊዝም እንዳለ ይቀጥል ወይስ ይሻሻል ወይስ አሃዳዊ ወደ ሆነው የመንግስት ስርዓት ይቀየር በሚለው ላይ ሰፋፊ የውይይት መድረኮች እያዘጋጁ ነው።

## ዋና ዋና ግኝቶች

- ከ10ሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች ስድስቱ ኢትዮጵያውያን (ማለትም 61 በመቶዎቹ) በሀገሪቷ ከአሃዳዊ ይልቅ ፌደራላዊ መንግስት እንዲኖር ይመርጣሉ። ከአስሩ ወደ አራት የሚጠጉት (ማለትም 37 በመቶዎቹ) ደግሞ ፌደራሊዝምን ከፋፋይ አድርገው በማየት ሀገሪቷ ወደ አሃዳዊ መንግስትነት ብትቀየር ይሻሉ (ግራፍ 1)።

- የፌደራል መንግስት በሀገሪቷ የሚቀጥል ከሆነ፤ ኢትዮጵያዊያን በሁለት የተከፈለ ፍላጎት ወይም ምርጫ አላቸው። ግማሽ የሚሆኑት (49 በመቶዎቹ) በሀገሪቷ ያለው ብሄርን መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝምና በእርሱ የተዋቀሩት ክልሎች እንዲቀጥሉ ፍላጎት አላቸው። በተመሳሳይ ድርሻ (ማለትም 48 በመቶዎቹ) የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ የክልሎች አወቃቀር መልካ-ምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ቢያደርግ ይመርጣሉ (ግራፍ 2)።

    - ኑሯቸውን ከተማ ያደረጉ የጥናቱ ተሳታፊዎች የክልሎች አወቃቀር መልካ-ምድራዊ አቀማመጥ መሰረት ቢያደርግ በተነፃፃሪ ይመርጣሉ (54 በመቶዎቹ ሲደግፉ፤ 44 በመቶዎቹ ይቃወማሉ)። በገጠር የሚኖሩት ማለትም እምብዛም የብሄር ስብጥር እንደ ከተማ የሌላቸው፤ እየተተገበረ ያለው የብሄር ፌደራሊዝም ቢቀጥል ይሻሉ (51 በመቶ ሲደግፉ፤ 47 በመቶዎቹ ይቃወማሉ)።

Copyright ©Afrobarometer 2020

## የአፍሮ-ባሮሜትር ጥናቶች

አፍሮ ባሮ-ሜትር አፍሪካ ላይ ትኩረት ያደረገ ገለልተኛ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው። ይህ ተቋም ታማኝ የሆኑ መረጃዎችን በዋናነት ዲሞክራሲ፣ አስተዳደርና የኑሮ ጥራት ላይ በማሰባሰብ የካበተ ልምድ አፍርቷል። ተቋሙ ሰባት ዙር ጥናቶችን በ38 ሀገራት ላይ ከ1999 እስከ 2018 እ.ኤ.አ መስራት የቻለ ነው፡ ፡ ስምንተኛ ዙር ጥናት በ2019/2020 የተካሄደ ሲሆን፤ ከ35 ሀገራት በላይ ተሳትፈውበታል። የአፍሮ ባሮ-ሜትር ጥናቶች የሚያካሄዱት በዋናነት በገፅ-ለገፅ ቃለ-መጠይቅ ሲሆን፤ የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደት የጥናቱ ተሳታፊዎች በመረጡት አካባቢያዊ ቋንቋ ይሆናል። ጥናቱ የሚካሄደው ወካይ የሆነ የናሙና መጠን በመመደብ ነው።

በፍሪደም ሀውስ ድጋፍ የኢትዮጵያ አፍሮ ባሮ-ሜትር ቡድን የተመራው በአብከን-የአማካሪ ድርጅት ነው። ጥናቱ የተካሄደው 2400 ቃለ-መጠይቆችን ዕድሜአቸው 18ና ከዚያ በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በማሳተፍ፤ መረጃው ከታህሳስ እስከ ጥር 2020 እ.ኤ.አ ተሰባስቧል። የናሙናው መጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰራና ወካይነት ያለው ሲሆን፤ የስህተት ህዳጉ +/-2 መቶኛና የአስተማማኝነት ደረጃው 95 በመቶ ነው። የአፍሮ ባሮ-ሜትር ጥናት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የተካሄደው በ2013 እ.ኤ.አ ነበር።

## የግራፎች ዝርዝር

**ግራፍ 1፡ የኢትዮጵያ መንግስት አሁን እንዳለው ፌደራላዊ ሆኖ ይቀጥል ወይስ አሃዳዊ ይሁን?**

|ኢትዮጵያ | 2012




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርበላቸው የነበረው ጥያቄ፤** ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

ሀሳብ 1: በኢትዮጵያ ብዝሃነት የተነሳ ራሳቸውን የቻሉ የክልል መንግስታት ያሉት የፌዴራሊዝም ዓይነት አሁንም ለዚህ ሀገር የተሻለ የመንግስት ቅርጽ ነው።

ሀሳብ 2: ፌዴራሊዝም በጣም ከፋፋይና ለግጭቶች የሚዳርግ ስለሆነ የኢትዮጵያ የመንግስት ቅርጽ ማዕከላዊ መንግስት በውሳኔ ሰጪነት የበለጠ ኗይል ወደሚኖረው አሃዳዊነት የመንግስት ቅርጽ መለወጥ/መቀየር ኣለበት።

(የመቶኛ ድርሻው ለሁለቱም ሀሳቦች "እስማማለሁ" ወይም "በጣም እስማማለሁ" ያሉትን ይይዛል)

**ግራፍ 2፡ የፌደራሊዝም አይነት፡ ህብረ-ብሄራዊ/ብሔር ወይም መልካ-ምድራዊ አቀማመጥ** |ኢትዮጵያ | 2012




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርበላቸው የነበረው ጥያቄ፤** ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

ሀሳብ 1: ኢትዮጵያ በፌዴራል ሥርዓት የምትቀጥል ከሆነ ኣሁን ያለው ክልሎች የተሰየሙበት የብሄር ፌዴራሊዝም እንዳለ መቀጠል ኣለበት።

ሀሳብ 2: ኢትዮጵያ በፌዴራል ሥርዓት የምትቀጥል ከሆነ ኣሁን ያለው ክልሎች የተሰየሙበት የብሄር ፌዴራሊዝም እንዳለ መቀጠል ኣለበት።

(የመቶኛ ድርሻው ለሁለቱም ሀሳቦች "እስማማለሁ" ወይም "በጣም እስማማለሁ" ያሉትን ይይዛል)

Copyright ©Afrobarometer 2020 

**For more information, please contact:**

Mulu Teka
National Investigator
ABCON – Research & Consulting
Tel +251 973 077 414 , +251 115 531 470, +251 115 521 696, +251 115 537 061
mulu.mtg@gmail.com / info@abconltd.et
Addis Ababa, Ethiopia

Visit us online at:
www.abconltd.et
www.afrobarometer.org

Follow our releases on #Voices Africa.

/Afrobarometer @Afrobarometer

Copyright ©Afrobarometer 2020